የኢትዮጵያ ፌደራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ

# ፌደራል ነጋሪት ጋዜጣ

# FEDERAL NEGARIT GAZETTE

OF THE FEDERAL DEMOCRATIC REPUBLIC OF ETHIOPIA

ሃያ ሰባተኛ ዓመት ቁጥር ፴
አዲስ አበባ ሰኔ ፴ ቀን ፪ሺ፲፫ ዓ.ም

በኢትዮጵያ ፌደራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ
የሕዝብ ተወካዮች ምክር ቤት ጠባቂነት የወጣ

27th Year No 30th
ADDIS ABABA 7th July, 2021

**ማውጫ**

አዋጅ ቁጥር ፩ሺ፪፻፶፩/፪ሺ፲፫

የውጭ ኦዲት ድግግሞሽን ለማስቀረት የወጣ
የነጠላ ኦዲት አዋጅ………………ገጽ ፲፫ሺ፪፻፺፭

**Content**

Proclamation No.1251/2013

Single Audit Proclamation ……..........Page 13295

## አዋጅ ቁጥር ፩ሺ፪፻፶፩/፪ሺ፲፫

## የውጭ ኦዲት ድግግሞሽን ለማስቀረት የወጣ የነጠላ ኦዲት አዋጅ

የፌደራሉ መንግሥት ለክልሎች ለአስቸኳይ ጊዜ እርዳታ ለመልሶ ማቋቋምና ለልማት ማስፋፊያ እንደዚሁም ለሚያስፈልጋቸው ወጪ የሚያደርገውን ድጐማ በሚመለከት ኦዲትና ቁጥጥር የማድረግ በሕገ መንግሥቱ አንቀጽ ፺፬ (፪) ሥልጣን የተሰጠው በመሆኑ፣

የፌደራል መንግሥቱ ኦዲትና ቁጥጥር የማድረግ ሥልጣን በአዋጅ ቁጥር ፱፻፹፪/፪ሺ፰ (እንደተሻሻለው ፩ሺ፩፻፵፮ /፪ሺ፲፩) አንቀጽ ፲፮ ለፌደራል ዋና ኦዲተር መስሪያ ቤት በመሰጠቱ፣

በሌላ በኩል ደግሞ በክልል ደረጃ የየክልሎቹ ዋና ኦዲተ መስሪያ ቤቶች በክልሉ የበጀት አዋጅ የታወጀው ሂሣብ ኦዲት እንዲያደርጉ ማቋቋሚያ አዋጆቻቸው ተመሳሳይ ሥልጣን ኃላፊነት የተሰጣቸው በመሆኑ፣

## PROCLAMATION NO. 1251/2021

## SINGLE AUDIT PROCLAMATION ISSUED TO ELIMINATE REPEAT AUDIT

**WHERE AS**,it has been provided in Article 94 (2) of the Constitution that the Federal Government shall have the power to audit and inspect emergency grant rehabilitation and development assistance and loans as well as subsidy grants by Federal Government to states;

**WHERE AS,** this power of the Federal Government of auditing or causing to be audited accounts involving Federal grant and subsidy to States were given to the Office of Federal Auditor General as per Article 16 of Proclamation 982/2016 as amended by proclamation number 1146/2019 ;

**WHERE AS,** on the other hand, the offices of the Regional Auditors General were also mandated in their establishment proclamation to Audit all accounts proclaimed in the annual budget of their respective regions;

ይህ በየደረጃው ላሉ የኦዲት መስሪያ ቤቶች የተሰጣቸው ኃላፊነት ደግሞ አንድ ሂሳብ በፌደራልም ሆነ በክልል የዋና ኦዲተር መስሪያ ቤቶች ኦዲት የሚደረግበትን ሁኔታና ድግግሞሽን የሚፈጥር በመሆኑ፣

በአንፃሩ ይህ ድግግሞሽ በኦዲት ተደራጊ መስሪያ ቤቶች ላይ ከፍተኛ የሥራ ጫና ከማስከተሉም በላይ ለተመሳሳይ ሥራ በድጋሚ በሚውለው ጊዜና የሰው ኃይል ምክንያት አላስፈላጊ ወጪ በማድረጉ፣

ስለሆነም ይህንን ችግር ለማስወገድ እንደዚሁም በሀገር አቀፍ ደረጃ የኦዲት አሠራሩንና ሥርዓቱን ወጥ እና ደረጃውን የጠበቀ እንዲሆን በሕገ መንግሥቱ አንቀጽ ፶፭(፩) መሠረት ይህ የውጭ ኦዲት ድግግሞሽን የሚያስቀር የነጠላ ኦዲት አዋጅ ታውጇል፡፡

## ፩. <u>አጭር ርዕስ</u>

ይህ አዋጅ "የውጭ ኦዲት ድግግሞሽን ለማስቀረት የወጣ የነጠላ ኦዲት አዋጅ ቁጥር ፩ሺ፪፻፶፩/፪ሺ፲፫" ተብሎ ሊጠቀስ ይችላል፡፡

## ፪. <u>ትርጓሜ</u>

የቃሉ አግባብ ሌላ ትርጉም የሚያሰጠው ካልሆነ በስተቀር በዚህ አዋጅ ውስጥ:-

፩/ "ዋና ኦዲተር" ማለት የፌደራል ዋና ኦዲተር ነው፡፡

፪/ "የፌደራል ድጋፍ" ማለት የፌደራል መንግሥትና ተቋማት ለልማት ማስፋፊያ፣ለአስቸኳይ ጊዜ እርዳታና ለመልሶ ማቋቋም በብድርም ይሁን በእርዳታ የፌደራል ላልሆኑ ተቋማት የሚሰጡት ድጋፍ ነው ፣

**WHERE AS,** this power granted to Audit Offices at various levels has resulted in the possibility of one account being audited by both offices of the Federal and Regional Auditors General and thereby causing audits duplication;

**WHERE AS**, this duplication has put an immense pressure on auditee's and unnecessary cost incurred as a result of time and human resource invested for similar work duplication ;

**NOW, THEREFORE**, to eliminate this duplication and ensure Audits are carried out under uniform practices and procedures throughout the country, this proclamation of Single Audit which eliminates duplication of external audit has been issued as per Article 55(1) of the Constitution.

## 1. <u>Short Title</u>

This Proclamation may be cited as "Single Audit Proclamation No.1251/2021"

## 2. <u>Definitions</u>

In this Proclamation unless the context other wise Requires:

1/ "**Auditor General**"means the Federl Auditor General;

2/ "**Federal Support**" means support provided by Federal Government and its institutions to Regional States for emergency, rehabilitation and development assistance and loans as well as subsidies;

፫/ "ተቀባይነት ያገኘ የመንግሥት የኦዲት ደረጃ" ማለት በፌደራል ዋና ኦዲተር መስሪያ ቤት የወጣ የኢትዮጵያ መንግሥት የኦዲት ደረጃ ወይም በፌደራል ዋናው ኦዲተር መስሪያ ቤት ተቀባይነት ያገኘ የኦዲት ደረጃ ነው፤

፬/ "የፌደራል ያልሆነ ተቋም" ማለት የክልል መንግሥታት፣ በክልል መንግሥታት የተቋቋሙ ድርጅቶች፣ መንግሥታዊ ያልሆኑ ተቋማትና ማህበራት እንደዚሁም የግል ድርጅቶች ነው፤

፭/ "መንግሥታዊ ያልሆነ ተቋማት " ማለት:-

ሀ) ለሕዝብ ጥቅም ሲባል ሳይንሳዊ ምርምሮችን፣ ትምህርትን፣ እርዳታዎችንና ሌሎች ሰብዓዊ አገልግሎቶችን ለማስፋፋት የተቋቋመ/ሙ፤

ለ) ትርፍን ዓላማው አድርጐ ያልተቋቋመ ሰብ□ዊ ድርጅት፤

ሐ) በሥራው ሂደት ትርፍ ቢያገኝ እንኳን መልሶ የሚሰጠውን ማህበራዊና ሰብዓዊ አገልግሎቶችን ለማሻሻልና ለማስፋፋት የሚያውል፡፡

፮/ "ክልል" ማለት የአዲስ አበባ ከተማ እና የድሬዳዋ ከተማ አስተዳደሮችን ጨምሮ፤በኢትዮጵያ ፌደራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ ሕገ መንግሥት መሠረት የተቋቋሙ ክልል ነው፤

፯/ "ነጠላ ኦዲት" ማለት በዚህ አዋጅ አንቀጽ ፬ መሠረት የፌደራል ባልሆኑ ተቋማት ኦዲት ድግግሞሽን ለማስቀረት የሚካሄድ የፋይናንስና ሕጋዊነት ኦዲት ነው፤

፰/ "ፕሮግራም ኦዲት" ማለት የፌደራል ባልሆኑ ተቋማት ሂሣብ ላይ የሚካሄድ የፕሮግራምና ፕሮጄክት ኦዲት ነው፤

፱/ "ተቀባይ" ማለት የፌደራል ተቋም ያልሆነ በቀጥታ ከፌደራል መንግሥት ወይም ተቋማት የፌደራል ድጋፍ የተቀበለ ነው፤

3/"**Accepted Government Auditing Standard**" means Ethiopian Government Auditing Standard prepared by the Office of the Federal Auditor General or other Audit Standard acceptable to the Office of the Federal Auditor General.

4/ "**Non- Federal Entity**" means Regiona states, organizations established by Regional states, Non - Governmental organizations and Associations as well as private organizations;

5/ " **Non- Government Organization**" means

a) Organization carrying out scientific research, providing education, aid and other humanitarian services for the benefit of the general public;

b) Not established for profit humanitarian Organization;

c) Organization, which may generate profit but plow back the profit to improve and expand humanitarian services ;

6/"**Region"**mean Regions and including Addis Ababa and Dire Dawa city administrations established as per the Constitution of Federal Democratic Republic of Ethiopia;

7/ "**Single Audit**"means Financial and Regularity Audit to be carried out in non- Federal entity as per Article 4 of this Proclamation to eliminate duplication of Audit;

8/ "**Program Audit**"means a project and program audit to be carried out on accounts of non - Federal entity;

9/ "**Recipient"** means non-Federal entity that receives Federal support directly from Federal government or Federal entities.

፲/ "ሚኒስቴር" እና "ሚኒስትር" ማለት የገንዘብ ሚኒስቴር ወይም ሚኒስትር ነው፤

፲፩/ "የውስጥ ቁጥጥር" ማለት በእያንዳንዱ ተቋም የሥራ አመራር ተዘርግቶ ተዓማኒነት ያለው የፋይናንስ ሪፖርት፣ውጤታማና ስኬታማ አፈጻጸም ለማምጣት የሚዘረጋ የአሠራር ሥርዓት ነው፤

፲፪/ "ገለልተኛ ኦዲተር" ማለት የፌደራል ዋና ኦዲተር ወይም የክልል ዋና ኦዲተር ወይም በኢትዮጵያ ውስጥ የኦዲት ሥራ እንዲሠራ አግባብ ባለው አካል ፈቃድ የተሰጠው ኦዲተር ነው፡፡

## ፫. የነጠላ ኦዲት ዓላማ

፩/ የፌደራል ላልሆኑ ተቋማት የተሰጠ የፌደራል መንግሥት ድጋፍና ድጎማ አስተዳደር በቂ የውስጥ ቁጥጥር ሥርዓት እንዲዘረጋለትና የፋይናንስ አስተዳደሩም እንዲጠናከር ማስቻል፡፡

፪/ የፌደራል ባልሆኑ ተቋማት የሚተዳደር የፌደራል ድጋፍና ድጎማ ሂሳብ ኦዲት አንድ ወጥ ሥርዓት እንዲከተል ማስቻል፡፡

፫/ ውጤታማና የታለመለትን ዓላማ የሚያሳካ የኦዲት ሀብት አጠቃቀም እንዲኖር ማስቻል፡፡

፬/ የኦዲት ድግግሞሽን በማስቀረት በክልሎችና ሌሎች የፌደራል ድጋፍ ተቀባይ ተቋማት ላይ በተደራራቢ ኦዲት ምክንያት ሊከሰት ይችል የነበረውን ጫና መቀነስ፡፡

፭/ የፌደራል መንግሥት ድጋፍ ያደረጉ ተቋማት በዚህ አዋጅ መሠረት በሚደረግ የኦዲት ውጤት እምነት እንዲጥሉና እንዲጠቀሙ ማስቻል፡፡

10/"**Ministry"and"Minister**"means the Ministry of Finance and its Minister ;

11/ "**Internal Control"**means system of control designed and implemented by management of each entity to ensure reliability of financial reports, the effectiveness and efficiency of performance;

12/ " **Independent Auditor**" means Federal Auditor General or Regional Auditors General or Private Audit Firms that are authorized and licensed to provide audit service in Ethiopia.

## 3. Objective Of Single Audit

1/ Ensure that sufficient internal control and sound financial management systems are designed and implemented for the Federal support and subsidy provided to non-Federal entity.

2/ Ensure that uniform audit practice and Procedures are applied to the audit of Federal support and subsidy account administered by non-Federal entity.

3/ Ensure effective and efficient audit resource utilization.

4/ Reduce the Audit pressure on regional States and other federal support reciver entities by eliminating repeat audit practice.

5/ Build confidence of Federal support providers to rely on audits carried out in accordance with this Proclamation.

**፬. በነጠላ ኦዲት የሚሸፈኑ ሂሣቦች**

፩/ በአንድ የበጀት ዓመት ከብር ፭ ሚሊዮን (አምስት ሚሊዮን) በላይ ወይም ሌላ ሚኒስትሩ የሚወስኑት የገንዘብ መጠን የፌደራል ድጋፍ የተቀበለ የፌደራል ያልሆነ ተቋም በነጠላ ወይም በፕሮግራም ኦዲት ሂሳቡን ሊያስመረምር ይችላል ፡፡ ይሁንና የፌደራል ወይም የክልል ዋና ኦዲተር አስፈላጊ ሆኖ ሲያገኘው የገንዘቡ መጠን ከዚህ ቢያንስም ኦዲት ሊያደርግ ወይም ሊያስደርግ ይችላል፡፡

፪/ የፌደራል ድጋፍን ተቀብሎ ከአንድ በላይ ለሆኑ ፕሮግራሞች ያዋለ የፌደራል ያልሆነ ተቋም ሂሳቡን በነጠላ ኦዲት ያስመረምራል፡፡

፫/ የገንዘብ ሚኒስቴር ኦዲት ሊደረግ የሚገባውን ዝቅተኛ የፌደራል ድጋፍ መጠን በየሁለት ዓመቱ አንድ ጊዜ ይከልሳል ፡፡ ነገር ግን በዚህ መሠረት የሚደርስበት ዝቅተኛው የገንዘብ መጠን ከብር ፭ (አምስት ሚሊዮን) በታች መሆን የለበትም፡፡

፬/ ከኦዲት ነፃ ከሚሆነው ዝቅተኛ የገንዘብ መጠን በላይ የፌደራል ድጋፍ ያገኘ የፌደራል ያልሆነ ተቋም ሂሳቡን በገለልተኛ ኦዲተር በየዓመቱ ያስመምራል፡፡

፭/ የፌደራል ድጋፍ የተቀበለ የፌደራል ያልሆነ ተቋም ሂሳብ ኦዲት ሲደረግ ተቀባይነት ያገኘ የመንግሥት የኦዲት ደረጃን ተከትሎ ወይም እንደነገሩ ሁኔታ የፌደራል ዋና ኦዲተሩ በሚወስነው መሠረት ይሆናል፡፡

**4. Accounts To Be Covered By Single Audit**

1/ Non- Federal entity receiving above (5,000,000) Five Million Birr in one particular Budget year or any other such amount to be determined by the Minister is required to have its account audited by either single audit or program audit. However, Federal or Regional Audit Office may decide to audit or cause to be audited, when deemed necessary, even if the amount is lower than the one set by the Minister.

2/ single audit shall be used when non- Federal entity use the Federal support to finance more than one program.

3/ Ministry of Finance shall determine on bi-annual basis the amounts of federal support which will be subject to an audit. however, such a minimum amount shall not be set at any time below (5,000,000) Five Million birr.

4/ All Non-Federal Entity that receives Federal support above the minimum amount of money determined shall be subject to audit and is required to get its account audited by independent Auditor.

5/Accounts of Non-Federal Entity that has received Federal support shall be audited in accordance with Generally Acceptable Government Auditing standard or such other standards to be determined and acceptable by the Federal Auditor General.

፮/ የፌደራል ድጋፍ ሂሳብ የነጠላ ወይም ፕሮግራም ኦዲት የሚደረገው:-

ሀ) በፌደራል ዋና ኦዲተር፣

ለ) በክልል ዋና ኦዲተሮች፣ ወይም

ሐ) በኢትዮጵያ ውስጥ የሂሳብ ምርመራ እንዲያደርጉ በሕግ የተቋቋሙ ወይም ፈቃድ በተሰጣቸው የግል ኦዲተሮች፣

ሊሆን ይችላል፡፡

፯/ በማንኛውም ጊዜና ተቋም ላይ የሚካሄድ የነጠላ ኦዲት የፌደራል ያልሆነውን ተቋም አጠቃላይ ሂሣብ መሸፈን አለበት፡፡

፰/ የነጠላ ወይም የፕሮግራም ኦዲት የሚያከናውን ገለልተኛ ኦዲተር:-

ሀ) የተዘጋጀው የሂሳብ መግለጫ ትክክለኛና በዓለም አቀፍ ደረጃ ተቀባይነት ካለው የሂሳብ አያያዝ መርህ ጋር የሚጣጣም መሆኑን ያረጋግጣል፣

ለ) በቂ የውስጥ ቁጥጥር ሥርዓት የተዘረጋና ሥራ ላይ የዋለ መሆኑን፣

ሐ) ከፌደራል ድጋፍ ጋር የተያያዘ የውል ስምምነቶች፣ እንደዚሁም ሌሎች አግባብ ያላቸውና ተፈፃሚ የሚሆኑ የፌደራልና የክልል ሕጎችና ደንቦች መከበራቸውን፣

መ) ከ ሀ-ሐ የተዘረዘሩትን ገምግሞ ካረጋገጠ በኋላ የተካሄደውን የኦዲት ሥራ ውጤት ለፌደራል ዋና ኦዲተር ሪፖርት ያቀርባል፣

ሠ) ሪፖርቱም የኦዲት ተደራጊው የሂሳብ መግለጫ ላይ የተሰጠውን አስተያየት፣ የውስጥ ቁጥጥር ሁኔታና አፈጻጸም እንደዚሁም ሕጐችና ደንቦች ስለመከበራቸው ሊያመለክት ይገባል፡፡

6/ Single or program audit on Federal support account may be carried out by

a) Federal Auditor General;

b) Regional Auditors General ;or

c) Such private audit firms authorized and licensed to provide audit services in Ethiopia.

7/ Single audits on any entity or period shall cover the entire operation of non- Federal entity.

8/An independent auditor who conducts single or program audit :

a) Shall confirm that accounts were prepared in accordance with Internationally accepted accounting standards;

b) Ensure sufficient internal control systems were designed and implemented;

c) Ensure compliance with terms of Federal upport contract and other relevant Federal and State laws and regulations;

d) Shall prepare and present report to Federal Auditor General office after reviewing condition set above in ‘a’ to ‘c’;

e) Auditor’s report shall contain opinion provided on auditee’s accounts, internal control situation and its implementation as well as compliance with laws and regulations.

**፭. <u>የነጠላ እና የሌሎች ኦዲቶች ግንኙነት</u>**

፩/ በዚህ አዋጅ መሠረት የሚካሄድ የነጠላ ኦዲት በሌሎች የፌደራል ሕጐች ሊደረግ የሚገባውን የፌደራል ያልሆነና የፌደራል ድጋፍ የተቀበለን ተቋም የፋይናንስ እና የሕጋዊነት ኦዲት ይተካል፣ ድጋፉን ያደረገው የፌደራል ተቋም በፌደራል ሕጐችና ደንቦች መሠረት ኃላፊነቱን ለመወጣት የሚያስችለውን መረጃ ከነጠላ ኦዲት ውጤት ማግኘት እስከቻለ ድረስ በዚሁ ላይ እምነት ሊጥልና ሊጠቀም ይችላል፡፡

፪/ በአንቀጽ ፭ ንዑስ አንቀጽ (፩) የተጠቀሰው ቢኖርም ድጋፉን ያደረገው የፌደራል ተቋም አስፈላጊ ሆኖ ሲያገኝ ሌላ ወይም ተጨማሪ ኦዲት እንዲደረግ ሊያደርግ ይችላል፡፡ማንኛውም የፌደራል ድጋፍ የተቀበለ ተቋም ድጋፍ አድራጊው የፌደራል ተቋም ተጨማሪ ኦዲት እንዲደረግ ወይም እንዲካሄድ ቢያደርግ ሊከለክል ወይም እግድ ሊጥል አይችልም፡፡

፫/ በዚህ አዋጅ ውስጥ የተመለከቱት ድንጋጌዎች በማንኛውም ዓይነት ሁኔታ ድጋፍ አድራጊው የፌደራል ተቋም ኦዲት ለማስደረግ ወይንም የፌደራል ድጋፉን ውጤታማነት ለመገምገም ያለውን መብት ወይም የፌደራል ዋና ኦዲተር ይህንን ሂሳብ ለመመርመር ቢፈልግ ገደብ የሚጥሉ አይደሉም፡፡

፬/ ድጋፍ አድራጊው የፌደራል ተቋም በነጠላ ኦዲት የተሸፈነውን ሂሳብ ኦዲት ማድረግ ቢወስን ለተጨማሪው ኦዲት ማካሄጃ የሚያስፈልገውን ወጪ በሙሉ ይሸፍናል፣ ሆኖም ተጨማሪው ኦዲት እንዲደረግ የወሰነ አካል ድግግሞሽን ለማስቀረት በፌደራል ዋና ኦዲተር ሲታመንበት ብቻ ይሆናል፡፡

፭/ የነጠላ ኦዲቱን ያከናወነ ገለልተኛ ኦዲተር በድጋፍ አድራጊው የፌደራል ተቋም ወይም በፌደራል በዋና ኦዲተር ሲጠየቅ የኦዲት የሥራ ወረቀቶችን ሲሆን ፎቶ ኮፒ ጭምር በመስጠት የመተባበር ግዴታ አለበት፡፡

**5. <u>Relationship Between Sinigle And Other Audits</u>**

1/ Single audits conducted in accordance with this Proclamation shall serve all other audit requirements as per other Federal laws.so long as support providing Federal entity obtains sufficient information from reports of single audit that is useful to discharge its duties under federal laws and regulations, it shall place reliance on single audit and may use the same.

2/ Notwithstanding the provisions of article 5 sub-Article (1) above, where appropriate the support providing Federal entity may cause other or additional audits. When support providing Federal entity request for such additional audit the Federal support recipient shall in any way co-operate.

3/ Provisions of this Proclamation shall not have the power to limit Federal entities'right to assess effectiveness of the program or Federal Auditor's General ability to audit such accounts;

4/ where support providing Federal entity decides to make further audit of accounts covered by single audit, it shall bear all related expenses; however,the repeated audit shall be conducted only when it's authorized of Federal Auditor General.

5/ Independent Auditor who has undertaken the single aud it has the duty to co-operate in availing audit working paper and shall also provide photo copies of such working paper if requested.

**፮. <u>የፌደራል ዋና ኦዲተር ኃላፊነት</u>**

፩/ የፌደራል ድጋፍና ድጎማ በተቀበለ ተቋም ሂሳብ ላይ የነጠላ ኦዲቱ በሌሎች ገለልተኛ ኦዲተሮች ሲከናወን በፌደራል ዋና ኦዲተር መ/ቤት በወጣው የመንግሥት የኦዲት ደረጃ ወይም በፌደራል ዋናው ኦዲተር ተቀባይነት ባገኘ ሌላ የኦዲት ደረጃ መሠረት ጥራቱን ጠብቆ መካሄዱን ይከታተላል፣ ይቆጣጠራል፡፡

፪/ የፌደራል ድጋፍን በሚመለከት የድጋፍ ሂሳቡን ነጠላ ኦዲት ያደርጋል፣ ያስደርጋል፡፡

፫/ በነጠላ ኦዲት የተሸፈነውን የድጋፍ ሂሳብ ኦዲት ውጤቶችን ለሕዝብ ተወካዮች በሚያቀርበው ዘገባ ውስጥ ያካትታል፡፡

**፯. <u>ድጋፍ አድራጊ የፌደራል ተቋማት ኃላፊነት</u>**

፩/ የፌደራል ድጋፍ ሂሳብ በነጠላ ወይም ፕሮግራም ኦዲት ወይም በሌሎች አግባብ ያላቸው የፌደራልና የክልል ሕጎችና ደንቦች መሠረት ኦዲት ያስደርጋል፡፡

፪/ በኦዲቱ ሂደት የሚገኙ ግኝቶችን አስመልክቶ የማስተካከያ እርምጃ ለመውሰድ የሚያስችል መርሀ ግብር ከኦዲት ተደራጊው የፌደራል ድጋፍ ተቀባይ ተቋም ጋር በመሆን ይነድፋል፣ ተግባራዊም ያደርጋል፡፡

**፰. <u>የመተባበር ግዴታ</u>**

ለዚህ አዋጅ ሥራ ላይ መዋል ድጋፍ አድራጊው የፌደራል ተቋምና ድጋፍ ተቀባዮች የመተባበር ግዴታ አለባቸው፡፡

**፱. <u>የኦዲት ባለሙያዎች የሙያ ሥነ-ምግባር</u>**

የነጠላ ኦዲቱን የሚያከናውን ማንኛውም ገለልተኛ ኦዲተር የፌደራል ዋና ኦዲተሩ የሚያወጣውን የሙያ ሥነ -ምግባር አክብረው የመሥራት ግዴታ አለባቸው፡፡

**6. <u>Responsibilities Of The Federal Auditor General</u>**

1/ Shall follow up and monitor the single audit undertaken by an Independent Auditor to ensure that audit has been executed in accordance with acceptable Government Auditing Standard or other standards accepted by the Federal Auditor General.

2/ Audit or cause to be audited Federal support account under single audit provisions.

3/ Shall incorporate the findings of Federal support accounts audit covered under single audit in its report to the House of Peoples' Representatives.

**7. <u>Responsiblities Of Federal Support Providing Entities</u>**

1/ Shall cause the audit of the Federal support accounts in accordance with single or program audit or other relevant Federal and State laws and regulations.

2/ Shall design and implement corrective action Plan in co-operation with Federal support receiving auditee entities to rectify audit findings identified during single audit.

**8. <u>Duties To Co-Operate</u>**

For effective implementation of this Proclamation both Federal support providing entities and recipients shall have the duty to co-operate.

**9. <u>Auditor's Code Of Conduct</u>**

Any Auditor undertaking single audit shall comply with Professional Code of Ethics issued by the Federal Auditor General.

## ፲. ጥፋትና ቅጣት

፩/ ማንኛውም ሰው:-

ሀ) የፌደራልና የክልል ዋናው ኦዲተር ወይም የግል ኦዲት ድርጅቶች በቀጥታ ወይም በኦዲተሮቹ ወይም በወኪሎቹ አማካይነት ለኦዲት እንዲቀርብለት የሚጠይቀውን መጻሕፍት ፣መዘክሮች፣ መዝገቦች፣ ሰነዶችና ሌሎች የጽሁፍ ወይም የቃል መረጃዎች ያላቀረበ፣

ለ) ለፌደራልና ክልል ዋናው ኦዲተሮች ወይም ሂሣቡን ኦዲት የሚያደርጉ የግል የኦዲት ድርጅቶች ለመሥሪያ ቤቶቹ ኦዲተሮች ወይም ለወኪሎች ሀሰተኛ መሆኑን እያወቀ ሀሰተኛ መረጃ የሰጠ ወይም እውነተኛ መሆኑን ለማመን ምክንያት ሳይኖረው ማናቸውንም መረጃ የሰጠ ፣

ሐ) የነጠላ ኦዲቱ ሥራ በሚገባ እንዳይከናወን ያሰናከለ ፣ ወይም

መ) ያለበቂ ምክንያት ሂሣቡን ኦዲት ባደረጉት ኦዲተሮች በቀረቡ ኦዲት ሪፖርቶች በተሰጡ የማሻሻያ አስተያየቶችና ሃሣቦች ላይ በ፲፭ ቀናት(አሥራ አምስት) ውስጥ እርምጃ ያልወሰደ፣ ወይም በዚህ አዋጅ በተደነገገው መሠረት መፈፀም ሲኖርበት ለመፈጸም ፈቃደኛ ሆኖ ያልተገኘ፣

እንደሆነ ከአምስት እስከ ሰባት ዓመት በሚደርስ እሥራት ወይም ብር ፲ ሺህ (አሥር ሺህ ብር) የገንዘብ መቀጫ ወይም በሁለቱም ይቀጣል፡፡

፪/ ማንኛውም ኦዲተር:-

ሀ) የሥራ ግዴታውን ለመፈጸም ወይም በኃላፊነቱ ወይም በሥራ ግዴታው ማድረግ የሚገባውን ላለማድረግ ወይም ማድረግ የማይገባውን ለማድረግ ስጦታ፣ ገንዘብ ወይም ሌላ ጥቅም እንዲሰጠው የጠየቀ፣ የተስፋ ቃል የተቀበለ ወይም የቀረበለትን የወሰደ፣

## 10. Offences And Penalty

1/Any person who:

a) fails to produce or make available books, documents, ledgers, vouchers or any other documentary or oral evidence which the Federal or Regional Auditors General or Private Audit Firms requests directly or through their employees or their representatives for auditing;

b) Gives to the Federal or the Regional Auditors General or Private Audit Firms who requests directly or through their employees or their representatives any information which he knows to be false or which he has no reason to believe to be true;

c) Obstructs the proper carrying out of the Single Audit; or

d) Fails to take measures on recommendations and comments included in the audit report; within 15(fifteen) days or fails to comply with the provisions of this Proclamation;

shall be punished with imprisonment from 5 (five ) to 7 (Seven) years or with a fine of Birr 10,000 (Ten Thousand Birr) or with both such fine and imprisonment.

2/ Any Auditor who:

a) Inconsideration for the performance or for the omission of an act in violation of the duties proper to his office solicits, exacts a promise of or receives a gift, money or any other advantage;

**ለ)** ለሚያደርገው የሂሣብ ምርመራ ተመርማሪው ያቀረበለት ሰነድ ሐሰተኛ መሆኑን እያወቀ እንደ ትክክለኛ ሰነድ ከያዘለት ወይም ትክክለኛነቱን እያወቀ ሊይዝ የሚገባውን በሰነድ ሳይቀበል የቀረ፣

ሐ) የፌደራል ወይም የክልል መንግሥት ገንዘብ ያጭበረበረ ወይም ሌላ ሰው እንዲያጭበረብር ሁኔታዎችን በማመቻቸት የተባበረ ወይም ያሴረ፣ወይም

**መ)** ተገቢ ያልሆነ ጥቅም ለራሱ ለማግኘት ወይም ለሌላ ሰው ለማስገኘት ወይም ሌላ ሰውን ለመጉዳት በማሰብ ፣ በተመርማሪው የቀረቡለትን መጻሕፍት፣ መዘክሮች፣ መዝገቦች፣ ሰነዶችና ሌሎች ማናቸውንም መረጃዎች እንዲጠፉ ያደረገ ወይም ወደ ሐሰት የለወጠ ወይም እንዲለወጡ ያደረገ

እንደሆነ ከ፭ (አምስት) እስከ ፲ (አሥር) ዓመት በሚደርስ እሥራት እና ከብር ፲ ሺህ እስከ ብር ፲፭ ሺህ (ከብር አሥር እስከ ብር አሥራ አምስት ሺህ) በሚደርስ የገንዘብ መቀጫ ይቀጣል፡፡

**፲፩. <u>መመሪያ የማውጣት ሥልጣን</u>**

የፌደራል ዋናው ኦዲተር መሥሪያ ቤት ለዚህ አዋጅ አፈፃፀም አስፈላጊ የሆነ መመሪያዎችን ከክልል ዋና ኦዲተር መስሪያ ቤቶች ጋር በመመካከር ሊያወጣ ይችላል፡፡

**፲፪. <u>አዋጁ የሚፀናበት ጊዜ</u>**

ይህ አዋጅ በፌደራል ነጋሪት ጋዜጣ ታትሞ ከወጣበት ቀን ጀምሮ የጸና ይሆናል።

**አዲስ አበባ ሰኔ ፴ ቀን ፪ሺ፲፫ ዓ.ም**

**ሳህለወርቅ ዘውዴ**

**የኢትዮጵያ ፌደራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ ፕሬዚዳንት**



b) Accepts any auditable document as genuine where he knows that it is not or unduly rejects any valuable document submitted to him by the one to be audited;

c) Defrauds or co-operates with others by creating conducive conditions so that they can defraud or conspires in defrauding money of the Federal or Regional Government; or

d) With intent to obtain or procure undue advantage for himself or to a third person or to cause a harm on any other person, causes to disappear or falsify or cause to be falsified or forges any books, documents, ledgers, vouchers or any other evidence submitted to him by the one to be audited ;

shall be punished with imprisonment from 5(five) to 10(Ten) years or with a fine of Birr 10,000 to 15,000 (Ten Thousand to Fifteen Thousand Birr).

**11. <u>Power To Issue Directive</u>**

For effective implementation of this proclamation in consultation with the Regional Auditor General Officies the Office of the Federal Auditor General is authorized to issue Directives.

**12. <u>Effective Date</u>**

This Proclamation shall enter into force from the date of publication in the Federal Negarit Gazette

**Done at Addis Ababa, on this day 7th of July, 2021**

**SAHLEWORK ZEWDIE**

**PRESIDENT OF THE FEDERAL DEMOCRATIC REPUBLIC OF ETHIOPIA**